# የኢትዮጵያ ወንጌላዊት ቤተ ክርስቲያን ሜነሶታ የተልዕኮ ሥልጠና

# ነሐሴ 4-9/2026

# ክፍል አንድ

# ኢየሱስና ታላቁ ተልዕኮ

***መግቢያ***

ክርስቲያናዊ ተልዕኮ በኢየሱስ ክርስቶስ ሕይወት፣ ሞት፣ ትንሣኤና ትእዛዝ ላይ የተመሠረተ ነው። ኢየሱስ ስለ ተልዕኮ ብቻ አላስተማረም፤ ተልዕኮን ኖረ። የጠፉትን ፈለገ፣ የተገለሉትን ቀረበ፣ የመንግሥቱን ወንጌል አወጀ፣ ደቀ መዛሙርትን አዘጋጀ፣ ሕይወቱንም ስለ ብዙዎች ቤዛ ሰጠ። ከትንሣኤው በኋላ ደቀ መዛሙርቱን ወደ ሕዝቦች ሁሉ ላከ። ተልዕኮ ለጥቂት ሚስዮናውያን ብቻ አልተሰጠም። ለመላዋ ቤተ ክርስቲያንና ለእያንዳንዱ የክርስቶስ ተከታይ ተሰጥቷል።

## I. ኢየሱስና ተልዕኮው

## 1. ኢየሱስ የተላከ አዳኝ ነው

ኢየሱስ ወደ ዓለም የመጣው በግልጽ ዓላማ ነው። እርሱ ከአብ የተላከ ነው። በዮሐንስ 20፥21 ኢየሱስ፡- "አብ እንደ ላከኝ እኔም እልካችኋለሁ።" ብሎ ተናገረ። የኢየሱስ ተልዕኮ፡- የእግዚአብሔርን መንግሥት ማወጅ፣ የጠፉትን መፈለግ፣ ኃጢአተኞችን ማዳን፣ የተሰበሩትን መፈወስ፣ የታሰሩትን ነፃ ማውጣት፣ የተገለሉትን መቀበል፣ ደቀ መዛሙርትን ማዘጋጀት፣ ሕይወቱን ቤዛ መስጠት ነበር።

## 2. የኢየሱስ ተልዕኮ መግለጫ

ሉቃስ 4፥18–19

ኢየሱስ በናዝሬት ምኩራብ ውስጥ የኢሳይያስን መጽሐፍ አንብቦ የተልዕኮውን ዓላማ ገለጠ። "የጌታ መንፈስ በእኔ ላይ ነው፤ ለድሆች ወንጌልን እንድሰብክ ቀብቶኛልና።" የኢየሱስ ተልዕኮ ቃልንና ተግባርን ያጣመረ ነበር።

2.1 ኢየሱስ የጠፉትን ፈለገ

ሉቃስ 19፥10

"የሰው ልጅ የጠፋውን ሊፈልግና ሊያድን መጥቶአልና።"

ኢየሱስ ሰዎች ወደ እርሱ እስኪመጡ ብቻ አልጠበቀም። ወደ እነርሱ ሄደ። የኢየሱስ ተከታይ እንደመሆናችን ሰዎች ወደ እኛ እስኪመጡ ብቻ አንጠብቅም። ያሉበት ድረስ በመሄድ ወንጌል እንሰብክላቸዋለን እንጂ።

2.2 ኢየሱስ ድንበር ተሻገረ

ኢየሱስ የብሔር፣ የባህል፣ የጾታ፣ የማኅበራዊ ደረጃና የሃይማኖት ድንበሮችን ተሻገረ።

ዮሐንስ 4፥4–42

ኢየሱስ ከሳምራዊቷ ሴት ጋር ሲነጋገር፦ የአይሁድና የሳምራውያንን ጥላቻ ተሻገረ፣ የወንድና የሴትን ማኅበራዊ ድንበር ተሻገረ፣ የሴቲቱን ታሪክ ሳያዋርዳት ገለጠ፣ እውነትንና ጸጋን አጣመረ፣ የሕይወት ውኃ እንደሚሰጥ ገለጠ።

ሴቲቱም ምስክር ሆና ወደ ከተማዋ ተመለሰች። ብዙ ሳምራውያን በምስክርነቷ ወደ ኢየሱስ መጡ።

ከጌታ የምንማረው፦ የሌላ ባህል ሰዎችን ማክበር፣ ከመናገር በፊት ማዳመጥ፣ እውነትን በፍቅር መናገር፣ ባህላዊ ኩራትንና ፍርድን መተው እንዳለብን ነው።

### 2.3 ኢየሱስ ሕዝቡን በምሕረት አየ

ማቴዎስ 9፥35–38

ኢየሱስ በከተሞችና በመንደሮች ዞሮ፦ አስተማረ፣ የመንግሥቱን ወንጌል ሰበከ፣ በሽተኞችን ፈወሰ፣ ዐዘነላቸው። ከዚያም፦ “መከሩ ብዙ ነው፤ ሠራተኞች ግን ጥቂቶች ናቸው።” አለ።

**ወሳኝ** የተልዕኮ እርምጃዎች፦ ሰዎችን በኢየሱስ ዓይን ማየት፣ ለእነርሱ መራራት፣ የመከሩ ጌታ ሠራተኞችን እንዲልክ መጸለይ፣ እኛም ለመላክ ዝግጁ መሆን።

### 2.4 ኢየሱስ ደቀ መዛሙርትን ጠራ

ማቴዎስ 4፥19

“ተከተሉኝ፤ ሰዎችንም አጥማጆች አደርጋችኋለሁ።” ይህ ጥሪ ሦስት ዋና ክፍሎች አሉት፦ ኢየሱስን መከተል፣ በኢየሱስ መለወጥ፣ በኢየሱስ ተልዕኮ መሳተፍ።

ማርቆስ 3፥13–15

ኢየሱስ አሥራ ሁለቱን የመረጠው፦ ከእርሱ ጋር እንዲሆኑ፣ ለስብከት እንዲላኩ፣ መንፈሳዊ ሥልጣን እንዲኖራቸው ነበር።

ተልዕኮ መጀመሪያ ከኢየሱስ ጋር ከመሆን ይጀምራል፤ ከዚያም ወደ ሰዎች በመላክ ይቀጥላል። ከኢየሱስ ጋር ሳንሆን ለኢየሱስ ሥራ ለመሥራት መሞከር የለብንም።

### 3. መስቀል፦ የኢየሱስ ተልዕኮ ማዕከል

ማርቆስ 10፥45

“የሰው ልጅ ሊያገለግልና ነፍሱን ስለ ብዙዎች ቤዛ ሊሰጥ እንጂ እንዲያገለግሉት አልመጣም።”

የኢየሱስ ተልዕኮ በመስቀል ወደ ፍጻሜው ደረሰ። ተልዕኮ ማለት የክርስቶስን ሞትና ትንሣኤ ለሕዝቦች ማወጅ ነው።

### 4. ትንሣኤ፦ የተልዕኮው ሥልጣንና ተስፋ

ትንሣኤው፦ ኢየሱስ ጌታ መሆኑን ያሳያል። ሞት መሸነፉን ያሳያል። ወንጌል እውነት መሆኑን ያረጋግጣል። ለአማኞች ዘላለማዊ ተስፋን ይሰጣል። ለተልዕኮ ድፍረትን ይሰጣል። ታላቁ ተልዕኮ የተሰጠው በተሰቀለውና በተነሣው ጌታ ነው!

# II. ታላቁ ተልዕኮ

## 1. ለአማኝ ሁሉ የተሰጠ ትዕዛዝ ነው

ጌታ ኢየሱስ የወንጌል ሥራን በተመለከተ ለደቀ መዛሙርቱም ሆነ  ዛሬ ለእኛ የሰጠው ተእዛዝ “ታላቁ ተልእኮ” ይባላል። ታላቁ ተልእኮ ጌታ ኢየሱስ በዓለም ሁሉ በእርሱ  ላመኑ ተከታዮቹ የሰጠው ትእዛዝ ነው። በዘርና በቋንቋ ሳይከፋፍል፣  ቦታና እውቀት ሳይለይ፣ የሙሉ ጊዜ አገልጋይና ምእመን ሳይል በእርሱ  ላመኑ ሁሉ የሰጠው ታላቅ ትእዛዝ ነው። ስለዚህ የጌታ ቤተ ሰብ የሆንን  ሁላችን ለታላቁ ተልእኮ ቅድሚያ ልንሰጥና የመኖራችን ዋና ዓላማ  ልናደርገው ይገባል።

በዘፍጥረት  መጽሐፍ እግዚአብሔር ለአብርሃምና ለዘሩ የሰጠውን ቃል ኪዳን  አምስት ጊዜ እንደ ደጋገመው፣ ታላቁ ተልእኮም አምስት ጊዜ በአዲስ  ኪዳን ውስጥ ተጽፎልን እናገኘዋለን። ሰዎች ብዙውን ጊዜ እንደ ታላቁ  ተልእኮ የሚረዱት በማቴዎስ 28 ያለውን ክፍል ብቻ ነው። እውነቱ  ግን በማርቆስ 16፣ በሉቃስ 24፣ በዮሐንስ 20 እንዲሁም በሐዋርያት  ሥራ 1 የታላቁን ተልእኮ ትእዛዝ እናገኛለን። እነዚህ አምስቱም የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች  የተልእኮውን የተለያዩ ገጽታዎች ያሳዩናል።

## 2. ታላቁ ተልዕኮ በአራቱ ወንጌላት

2.1 ማቴዎስ 28፥18–20 (ይህ ክፍል ዝቅ ብሎ ተብራርቷል)

ዋና ትኩረት፦ ሕዝቦችን ሁሉ ደቀ መዛሙርት ማድረግ ነው።

2.2 ማርቆስ 16፥15 “እንዲህም አላቸው። ወደ ዓለም ሁሉ ሂዱ ወንጌልንም ለፍጥረት ሁሉ ስበኩ።”

ዋና ትኩረት፦ ወንጌልን ለፍጥረት ሁሉ መስበክ ነው።

2.3 ሉቃስ 24፥46–49 “እንዲህም አላቸው። ክርስቶስ መከራ ይቀበላል በሦስተኛውም ቀን ከሙታን ይነሣል፥ በስሙም ንስሐና የኃጢአት ስርየት ከኢየሩሳሌም ጀምሮ በአሕዛብ ሁሉ ይሰበካል ተብሎ እንዲሁ ተጽፎአል። እናንተም ለዚህ ምስክሮች ናችሁ። እነሆም፥ አባቴ የሰጠውን ተስፋ እኔ እልክላችኋለሁ፤ እናንተ ግን ከላይ ኃይል እስክትለብሱ ድረስ በኢየሩሳሌም ከተማ ቆዩ።”

ዋና ትኩረት፦ የክርስቶስ መከራ፣ የክርስቶስ ትንሣኤ፣ ንስሐ፣ የኃጢአት ስርየት፣ ለአሕዛብ ሁሉ መስበክ፣ የመንፈስ ቅዱስን ኃይል መጠበቅ ነው።

2.4 ዮሐንስ 20፥21 “አብ እንደ ላከኝ እኔ ደግሞ እልካችኋለሁ አላቸው።”

ዋና ትኩረት፦ ኢየሱስ እንደተላከ እኛም መላክ ነው።

2.5 ሐዋርያት 1፥8 “ነገር ግን መንፈስ ቅዱስ በእናንተ ላይ በወረደ ጊዜ ኃይልን ትቀበላላችሁ፥ በኢየሩሳሌምም በይሁዳም ሁሉ በሰማርያም እስከ ምድር ዳርም ድረስ ምስክሮቼ ትሆናላችሁ አለ።”

ዋና ትኩረት፦ የመንፈስ ቅዱስ ኃይል፣ የክርስቶስ ምስክር መሆን፣ ከአካባቢ ወደ ምድር ዳርቻ መድረስ ነው።

## 3. ማቴዎስ 28፥18–20 ትንታኔ

“ኢየሱስም ቀርቦ፦ ሥልጣን ሁሉ በሰማይና በምድር ተሰጥቶኛል። ስለዚህ ሂዱና አሕዛብን ሁሉ በአብና በወልድና በመንፈስ ቅዱስ ስም እያጠመቃችኋቸው፣ ያዘዝኋችሁንም ሁሉ እንዲጠብቁ እያስተማራችኋቸው ደቀ መዛሙርት አድርጓቸው፤ እነሆም፣ እኔ እስከ ዓለም ፍጻሜ ድረስ ሁልጊዜ ከእናንተ ጋር ነኝ።”

### በዚህ ክፍል ውስጥ አምስት ዋና እውነቶች አሉ፦

1. የክርስቶስ ሥልጣን

*“ሥልጣን ሁሉ ተሰጥቶኛል”*

*ታላቁ ተልዕኮ በሰው ችሎታ አይጀምርም። በክርስቶስ ሥልጣን ይጀምራል። ጌታ ኢየሱስ በሰማይ፣ በምድር፣ በኃጢአት ላይ፣ በሞት ላይ፣ በመናፍስታዊ ኃይሎች ላይ፣ በህዝቦችና በመንግሥታት ላይ ባለሥልጣን ነው። ስለዚህ ወደ ሕዝቦች ስንሄድ ብቻችንን አንሄድም። በክርስቶስ ሥልጣን እንሄዳለን።*

2. *የመሄድ ጥሪ*

*“ሂዱ”*

*“ሂዱ” የሚለው ትእዛዝ፡- ከምቾት መውጣትን፣ ወደ ሰዎች መቅረብን፣ የባህል ድንበር መሻገርን፣ የቋንቋ ልዩነትን መቀበልን፣ ሰዎችን በፍቅር መቅረብን፣ ጌታ ወደሚልከን ቦታ መሄድን ያካትታል። ሁሉም ክርስቲያን ድንበር ተሻግሮ አይሄድም። ሁሉም ክርስቲያን ግን በሚኖርበት፣ በሚሠራበትና በሚሄድበት ሁሉ የክርስቶስ ምስክር ነው።*

3. *ሕዝቦችን ሁሉ መድረስ*

*“አህዛብን ሁሉ”*

*“ሕዝቦች” የሚለው ቃል ፖለቲካዊ አገሮችን ብቻ አያመለክትም። የሚያካትተው፡- ብሔሮች፣ ነገዶች፣ የቋንቋ ቡድኖች፣ ባህላዊ ማኅበረሰቦች፣ ማኅበራዊ ቡድኖች ነው። አንድ አገር ውስጥ ብዙ የተለያዩ ሕዝቦች ሊኖሩ ይችላሉ። አንድ አገር ወንጌልን ሰምቷል ማለት በዚያ አገር ያሉ ሕዝቦች ሁሉ ተደርሰዋል ማለት አይደለም። ለምሳሌ፡-ኢትዮጲያ ከ65% በላይ ክርስቲያን ነው። የወንጌል አማኝ ከ20% በላይ ነው። ዳሩ ግን በፕሮጀክት ዜሮ ጥናት መሰረት 43 የማህበረሰብ ክፍል በወንጌል አልተደረሰም።*

*የታላቁ ተልዕኮ ራዕይ በራዕይ 7፥9 ዮሐንስ፡- ከሕዝብ፣ ከነገድ፣ ከወገንና ከቋንቋ ሁሉ የመጡ ሰዎች በዙፋኑ ፊት ቆመው ሲያመልኩ አየ። ይህ የተልዕኮው የመጨረሻ ራዕይ ነው።*

4. *ደቀ መዛሙርትን የማድረግ ትእዛዝ*

*“ደቀ መዛሙርት አድርጉ”*

*የታላቁ ተልዕኮ ዋና ትእዛዝ “ደቀ መዛሙርት አድርጉ” የሚለው ነው።*

*ደቀ መዝሙር ማን ነው?*

*ደቀ መዝሙር፡- ኢየሱስን የሚከተል፣ በኢየሱስ የሚለወጥ፣ ቃሉን የሚማር፣ ትእዛዙን የሚፈጽም፣ በእምነት የሚኖር፣ ወንጌልን የሚያካፍል፣ ሌሎችን ደቀ መዛሙርት የሚያደርግ ሰው ነው።*

*ደቀ መዝሙር ማድረግ የሚያካትተው፡- ከሰዎች ጋር ግንኙነት መገንባት፣ ወንጌልን ማካፈል፣ ወደ ንስሐና ወደ እምነት መጥራት፣ አዲስ አማኞችን ማጥመቅ፣ ቃሉን ማስተማር፣ ታዛዥነትን ማሳደግ፣ በቤተ ክርስቲያን ማኅበረሰብ ውስጥ መታቀፍ፣ ሌሎችን ማገልገል ማስተማር፣ አዲስ መሪዎችን ማዘጋጀት፣ የሚባዙ ደቀ መዛሙርትን ማፍራት ነው። ወንጌልን አንድ ጊዜ መናገር የደቀ መዝሙርነት መጀመሪያ ነው፤ ፍጻሜው ግን አይደለም። ደቀ መዝሙርነት የየዕለት ኑሮ ነው።*

*“እንዲጠብቁ አስተምሩ”*

*ኢየሱስ “ያዘዝኋችሁን ሁሉ እንዲያውቁ” ብቻ አላለም። “እንዲጠብቁ አስተምሯቸው” ነው ያለው። የክርስቲያናዊ ትምህርት ግብ መረጃ ማስተላለፍ ብቻ አይደለም። ታዛዥነትን ማሳደግ ነው። የሕይወት ለውጥ ማምጣት ነው። የክርስቶስን ባሕርይ መልበስ ነው። ሌሎችን ለማገልገል መዘጋጀት ነው።*

5. የክርስቶስ አብሮነት

**"እኔ ከእናንተ ጋር ነኝ"**

*ታላቁ ተልዕኮ በታላቅ ተስፋ ይጠናቀቃል። "እነሆ፣ እኔ እስከ ዓለም ፍጻሜ ድረስ ሁልጊዜ ከእናንተ ጋር ነኝ።"*

*የኢየሱስ መገኘት ያበረታታናል። ተልዕኮውን ብቻችንን አንፈጽምም። የትንሣኤው ጌታ ከእኛ ጋር ነው።*

**የሚከተሉት አራት ነጥቦች ያልተጀመረውን እንድንጀምር እንዲሁም ያላለቀውን እንድንጨርስ ይረዱናል። እነዚህ እውነቶች ታላቁን ተልእኮ በአገራችንና በጎረቤት አገሮች ብቻ ሳይሆን፣ በሩቅ ላሉትም ሕዝቦች ወንጌል እንዲደርስ የእኛን ኃላፊነት እንድንወጣ ያግዙናል።**

1) **ጸሎት**

**ወንጌል ላልደረሳቸው ሕዝቦች ስንጸልይ ለሁለት ዋና ዋና ነገሮች እንጸልያለን። በመጀመሪያ ወንጌል ያልደረሳቸው የዚህ ዓለም ገዢ ዓይናቸውን አሳውሮ በጨለማው ግዛት ስለጠበቃቸው ነውና ጸሎታችን የክፉውን ኃይል በመስበር የሕዝቡ ዓይኖች እንዲከፈቱ፣ ለወንጌልም ልባቸው እንዲከፈት መሆን አለበት። ሁለተኛው ጸሎታችን ደግሞ የመከሩ ጌታ ወደ እነርሱ ሰዎችን የተልእኮ መልእክተኞች አድርጎ እንዲልክ ነው።**

**ጸሎት አገልግሎታችንን የሚያሳካልን መሣሪያ ብቻ ሳይሆን ራሱ አገልግሎታችን ነው። ምንም ያህል እቅድ ብናወጣ፣ የሠለጠነ የሰው ኃይል ብናሰማራ፣ የሚያስፈልገንን ሁሉ የሚያዘጋጁልን ባለሀብቶች ከጎናችን ሆነው ቢደግፉን ያለ እግዚአብሔር መንፈስ ርዳታ የታላቁ ተልእኮን ትእዛዝ መፈጸም አንችልም። ስለዚህ ጸሎት ዋናና ቁልፍ ሥራችን ነው።**

**የሚከተሉት የምክር አሳቦች የታላቁ ተልእኮ የጸሎት ሕይወታችን እንዲያድግ ሊረዱን ይችላሉ፡-**

- **በየቀኑ ወንጌል ላልደረሳቸው የሕዝብ ክፍሎች መጸለይ (ለዚህ ሊረዳን የሚችል መረጃ በዚህ መጽሐፍ በስተመጨረሻ ይገኛል)፤በሳምንት አንድ ጊዜ ካልሆነም በወር አንድ ጊዜ ከሌሎች የወንጌል አማኞች ጋር ተገናኝቶ ወንጌል ላልደረሰው ማኅበረ ሰብ መጸለይ፤**
- **በእሑድ የአምልኮ ጊዜ በየቤተ ክርስቲያኖቻችን ወንጌል ላልደረሰው፣ ለአንድ የሕዝብ ወገን መጸለይ (ለዚህ የሚጠቅም መረጃ በዚህ መጽሐፍ በስተመጨረሻ ይገኛል)፤**
- **የዓለምን ዜና ለታላቁ ተልእኮ ጸሎት እንደ መረጃ መጠቀም። ለምሳሌ በአንድ አገር ጥቃት ደርሶ ይህን ያህል ሰው ሞተ የሚል ዜና ስንሰማ ወዲያውኑ ወንጌል ወደዚያች አገር እንዲገባና ሰላም በምድሪቷ ውስጥ እንዲሰፍን መጸለይ፤**
- **የወንጌል መልእክተኛ ሆነው ወንጌልን ለሚያደርሱ የእግዚአብሔር ልጆች በመደበኛነት መጸለይ፤**
- **በመስጊድ የጸሎት ድምፅ ሲሰማ ወንጌል ለእስልምና ሃይማኖት ተከታዮች እንዲደርስና ልባቸው ለወንጌል ክፍት እንዲሆን መጸለይ፤**

## 2) ለታላቁ ተልእኮ ቅድሚያ እንስጥ

**ታላቁን ተልእኮ ለመፈጸም ከእግዚአብሔር ጋር ትርጉም ባለው መልኩ የሚተጉ የአማኞች ቍጥር ከመቶ አንድ ብቻ እንደ ሆነ ይነገራል። የቤተ ክርስቲያን ሥራ ሁሉ ታላቁ ተልእኮ አይደለም። በቤተ ክርስቲያናችንም ታላቁን ተልእኮ ብናስተምር ኃላፊነታችንን ተወጣን ማለት አይደለም። ጌታ ኢየሱስ ታላቁን ተልእኮ ለደቀ መዛሙርቱ ሲሰጣቸው፣ "ሕዝቦችን ሁሉ . . . ደቀ መዛሙርት አድርጓቸው" ነው ያላቸው።**

**ለምን ከመቶ አንድ ብቻ! ያልን እንደ ሆነ መልሱ ቅድሚያ የምንሰጣቸው ነገሮች በሕይወታችንና በቤተ ክርስቲያናችን ስለበዙና የ"ሕዝቦች" ጉዳይ ወደ ኋላ ስለተተወ ነው። ለዚህም መድኃኒቱ ጌታ ኢየሱስ ቅድሚያ የሰጠውን ጉዳይ እኛም በሕይወታችን ቀዳሚ ትኩረት መስጠት ነው። ጌታ ኢየሱስ የእኛ ታላቅ ወንድም ሆኖ የጠፋውን ሊፈልግ መጣ።**

ጌታ ኢየሱስ ለጠፉ ሰዎች ቅድሚያ ይሰጣል። ሰማይን ትቶ ወደ ምድር የመጣው ለእኛ ለጠፋነው ቅድሚያ ስለ ሰጠን ነው። በግል ሕይወታችን፣ በቤተ ክርስቲያናችንም ወንጌል ላልደረሳቸው ሰዎች ቅድሚያ ልንሰጣቸው ይገባል። ጊዜአችን፣ ገንዘባችን፣ መርሀ ግብሮቻችን ሁሉ ለታላቁ ተልእኮ ቅድሚያ መስጠታችንን የሚመሰክሩ ይሁኑ።

ቤተ ክርስቲያን ታላቁን ተልእኮ አስተምራ ወንዶችና ሴቶች ልጆችን ወንጌል ወዳልደረሳቸው ሰዎች በብዙ ቍጥር መላክ መጀመር አለባት። ወደ አሜሪካ ትሄዳለህ ብቻ ሳይሆን ወደ ሶማሊያ፣ ወደ የመን ትላካለህ ብለው የሚተነብዩ ነቢያትም እንዲነሡ መጸለይ ያስፈልጋል፤ እግዚአብሔር ሶማሌዎችና ዓረቦች በቋንቋቸው ሲያመልኩት መስማት ናፍቆታልና። ዛሬም "ማንን ልላክ? ማን ይሄድልኛል?" እያለ ነውና አዲስ ዘመን ይምጣልን። በብዙ መቶዎች የሚቈጠሩ ኢትዮጵውያንና ኤርትራውያን የወንጌል መልእክተኞች ሆነው ወንጌል ወዳልደረሳቸው ሕዝቦች፣ በክብር ለክቡር አገልግሎት የሚሄዱበት፣ ቤተ ክርስቲያንም ዓይኖቿን ከሕንፃና ከሌሎች ነገሮች ላይ አንሥታ መልእክተኞችን መላክ ላይ የምታተኩርበት ዘመን ይፍጠንልን።

## 3) ታላቁ ተልእኮ ዋጋ የሚያስከፍል ኃላፊነት ነው

ታላቁን ተልእኮ በሕይወታቸው የተገበሩት ሁሉ ፍሬ አፍርተዋል፤ ከዚህም የተነሣ ጠላት በብርቱ ተገዳድሯቸዋል። ሰይጣን ፍሬ ከማያፈራው ክርስቲያን ይልቅ ፍሬ የሚያፈራውን ይፈራል። የታላቁ ተልእኮን ፍሬ ደግሞ አብልጦ ይፈራዋል። ምክንያቱም ታላቁ ተልእኮን ስናሳካ የሰይጣንን ድንበር እየጣስን ነው። ለዘመናት በከፉዉ መንግሥት ውስጥ እስረኛ የነበሩትን ነው ነጻ የምናወጣውና ወደ ልጁ መንግሥት የምናፈልሰው። እናም ውጊያው ብርቱ ነው። በዚህ የታላቁ ተልእኮ አገልግሎት ውስጥ ሕይወታቸውን ያጡ፣ ለዘመናት በእስር የማቀቁ፣ ሀብት ንብረታቸው የተዘረፈባቸው፣ በአካላቸው ላይ ብዙ ጉዳት የደረሰባቸው፣ ከሚወድዷቸው ቤተ ሰቦቻቸው የተቆራረጡ፣ ከሥራ የተባረሩ፣ መጥፎ ስም የተሰጣቸው፣ የተሰደዱ፣ የሚበሉትና የሚጠጡት ያጡ፣ እንዲህ ያሉና ሌሎች መከራዎች የደረሱባቸው ብዙ ናቸው። ይሁን እንጂ ሐዋርያው ጳውሎስ እንዳለው፣ "የአሁኑ ዘመን ስቃያችን ወደ ፊት ሊገለጥ ካለው ለእኛ ከተጠበቀልን ክብር ጋር ሲነጻጸር ምንም እንዳይደለ እቈጥራለሁ" (ሮሜ 8፥18) ነው እውነቱ።

የታላቁ ተልእኮ ኃላፊነት ዋጋ ያስከፍል እንጂ ጠላት በከፋት ያደረገውን እግዚአብሔር ሁሌ ለክብሩ ይጠቀምበታል። በኢየሩሳሌም የነበረችው የመጀመሪያዋ ቤተ ክርስቲያን ብዙ መከራና ስደት ደርሶባታል። ወንጌል የምታስፋፋ ቤተ ክርስቲያን የሚገጥማት የጠላት ተግዳሮት ብዙ ነው። ከስደቶቹ ሁሉ የከፋው ስደት እስጢፋኖስ በድንጋይ ተወግሮ ከሞተ በኋላ የመጣው ነበር። መጽሐፍ ቅዱስ እስጢፋኖስ በድንጋይ በሚወገርበት ጊዜ ". . . በዚያ የነበሩት ምስክሮችም ልብሳቸውን ሳውል በተባለ ጎልማሳ እግር አጠገብ አስቀመጡ" (የሐሥ 7፥58) ይላል። ይህ ብቻ ሳይሆን "ሳውልም በእስጢፋኖስ መገደል ተስማምቶ ነበር" (የሐሥ 7፥60)። ጠላት አንድ የእግዚአብሔር መንግሥት ሠራተኛ ገደልኩ፤ ስደትንም አስነሣሁ ብሎ ደስ ሲለው፣ ለካስ እግዚአብሔር ይህንን ሁሉ ተጠቅሞ ክብሩን ሊገልጽ ወድዷል። ሳውል የጌታን ደቀ መዛሙርት ለመግደልና ለማሰር እየሮጠ ባለበት ጊዜ በደማስቆ መንገድ ጌታ ኢየሱስ አግኝቶ ማረከው፤ ልጁም አደረገው። እንዲያውም ለታላቁ ተልእኮ አገልግሎት ሾመው። የአምላክ ሥራ ድንቅ ነው! ለቤተ ክርስቲያን መሰደድ ምክንያት የሆነው ሳውል (ጳውሎስ) በአንጾኪያ ቤተ ክርስቲያን ለአንድ ዓመት ወንጌል አስተማረ። በኋላም የመጀመሪያ ሚስዮናዊ ሆኖ ለአሕዛብ ወንጌል እንዲያደርስ ከበርናባስ ጋር ከአንጾኪያ ቤተ ክርስቲያን ተላከ። የአንጾኪያ ቤተ ክርስቲያንም ለአሕዛብ አብያተ ክርስቲያናት እናት ቤተ ክርስቲያን ሆነች።

ጠላት ሳውልን የእግዚአብሔርን ቤተ ክርስቲያን ለማጥፋት ቢያነሣሣው፣ እስጢፋኖስ ቢሞት፤ ሌሎች ቢሰደዱ የሚታ ሚታ ግን አምላካችን አሳዳጁን ማርኮ በብዙ እጥፍ ወንጌል እንዲሰራጭና ቤተ ክርስቲያን ዓለምን እንድትሞላ አድርጓል። በእኛ ላይ የሚደርሰው መከራም ውሎ አድሮ የእግዚአብሔር የክብር መገለጫ ስለሚሆን የታላቁ ተልእኮ ኃላፊነት የሚያስከፍለንን ዋጋ ከፍለን ይህንን ክቡር ሥራ በሕይወት ዘመናችን ሳንታክት እንሥራ።

## 4)ታላቁ ተልእኮ ተነጣጥለን ሳይሆን ተባብረን የምንሠራው ነው

ታላቁ ተልእኮ ትልቅ ስለሆነ ብቻችንን ልንሠራው አንችልም፤ ከወንድምና እኅቶቻችን ጋር አብረን ልንሠራው ግድ ነው። ብዙ ጊዜ ለብቻ የሚሠሩ ሥራዎች ይዘወተራሉ። እንደ እግር ኳስ ባሉ የቡድን ስፖርቶች ደካሞች ሆነን እንደ ሩጫ ባሉት የግል ጥረቶች ጎበዞች የሆንነው ለዚህ ይሆን?

የታላቁን ተልእኮ ኃላፊነት ለመወጣት አብሮ መሥራት የግድ ነው። አብሮ መሥራት የሚመሠረተው በመተማመን ላይ ነው። መተማመን ከሌለ አብሮ ለመሥራት ከመነሣታችን በፊት መተማመንን ለማዳበር መሥራት ይኖርብናል። መተማመን አብሮ ለመሥራት መሠረታዊ ነገር ሆኖ ሳለ በቀላሉም ሊሰበር የሚችል ነው።

የሚከተሉትን ነጥቦች ማጤን ተባብሮ ለመስራት ይረዳል፦

- አብረው ሊሠሩ የተስማሙ አካላት ስምምነታቸውንና ገንዘባቸውን በተመለከተ ገቢና ወጪውን እንዲሁም የሥራ ውጤታቸውን በጽሑፍ መያዝ ከከረረ አለመግባባት ይጠብቃል፤
- ግልጽነትን ማጎልበት፤ ይህም ደግሞ አንዱ ሊሰማው የሚወድደውን ብቻ መንገር ሳይሆን፣ ስኬቱንም ውድቀቱንም በግልጽነት መነጋገር፣ አብሮም መፍትሔዎችን ማፈላለግ፤
- አብረው የሚሠሩ አካላት ከአገልግሎቱ ውጪ እየተገናኙ በሰፊው መተዋወቅንና መተማመንን ማዳበር፤
- በአንድ አካባቢ ያሉ አብያተ ክርስቲያናት በአንድነት የታላቁን ተልእኮ ሥራ ለመሥራት በመስማማት፣ ወንጌል ያልደረሰውን ሕዝብ በጸሎት መርጦ ያ ሕዝብ በወንጌል እስኪደረስ ድረስ ያላቸውን ሁሉ ወደ አንድነት በማምጣት መሥራት፤ የወንጌል መልእክተኞች ከመካከላቸው እንዲወጡ በጸሎትና በቃሉ ምእመናቸውን ማስተማር፤ ጌታ ለወንጌል የጠራቸውን ወንጌል ወዳልደረሳቸው ሕዝቦች መላክ።
- በትልልቅ ከተሞች ያሉ አብያተ ክርስቲያናት፣ በከተሞች ውስጥ ያለውን ረሃብ፣ ሱስ፣ ጎዳና ተዳዳሪነት፣ የመጠጥና የዝሙት ቤቶችን ቍጥር በመቀነሱ ረገድ ተጽእኖ ማምጣት እንዲቻል አብሮ መሥራት።
- አብያተ ክርስቲያናት በአንድነት የሚሲዮናዊ ጥሪ ያላቸውን ሰዎች በገንዘባቸው እየደገፉ ወደ ጎረቤት አገሮችና ከዛም ባለፈ ወደ ሌሎች ወንጌል ወዳልደረሳቸው ሕዝቦች መላክ።
- እንደ ግለ ሰብም ሆነ እንደ ቤተ ሰብ በነፍስ ወከፍ ጌታ ኢየሱስ ገና ወደ ማይታወቅበት ቦታ ወንጌል ይዘው የሚሄዱትን በገንዘብና በጸሎት ብንደግፍ ብዙ መሥራት እንችላለን።
- የታላቁ ተልእኮ ጥሪ ያላቸው መንፈሳዊ ድርጅቶችም እርስ በእርስ እየተገናኙ አንዱ የሚሠራውን ለሌላው ግልጽ ቢያደርግና በአላስፈላጊ የድግግሞሽ ሥራ ባይባክኑ፤ ገንዘባቸውም በአጋርነት እንዲሠራበት ቢመካከሩ ብዙ ትርፍ ይኖረዋል።

እነዚህ ነጥቦች ተቀራርበን እንዴት መሥራት እንችላለን በሚል ማሰብ እንድንጀምር ቢረዱን እንጂ ማድረግ የምንችለው ሌላ ብዙ ነገር ይኖራል። ታላቁ ተልእኮ ትልቅ ነውና ተነጣጥለን ልንወጣው አንችልም። የእግዚአብሔር መንግሥት ማንነታችንን መግዛት ከቻለ ራስ ወዳድነታችንን ወደጎን ጥለን፣ የቤተ ክርስቲያናችንንና የመንፈሳዊ ድርጅታችንን ስምና አርማ ወደ ጎን አድርገን፣ በአንድነት በእግዚአብሔር መንግሥት ጥላ ሥር ሆነን በመሥራት ይህንን የታላቁን ተልእኮ ሥራ ማፋጠን፣ መጨረስም እንችላለን።

## ማጠቃለያ

- ኢየሱስ ከአብ የተላከ አዳኝ ነው።
- የኢየሱስ ተልዕኮ የጠፉትን መፈለግና ማዳን ነው።
- ኢየሱስ ወንጌልን በቃልና በተግባር አሳየ።
- ሰዎችን በምሕረት አየ።
- የባህልና የማኅበራዊ ድንበሮችን ተሻገረ።
- ደቀ መዛሙርትን ጠራ፣ አሰለጠነና ላከ።

- ***መስቀልና ትንሣኤ የተልዕኮ መሠረት ናቸው።***
- ***ታላቁ ተልዕኮ በክርስቶስ ሥልጣን ተሰጥቷል።***
- ***ዋናው ትእዛዝ ሕዝቦችን ሁሉ ደቀ መዛሙርት ማድረግ ነው።***

# ክፍል ሁለት

# ዓለም አቀፍ ክርስቲያን መሆን

## 1. ዓለም አቀፍ ክርስቲያን ማን ነው?

ዓለም አቀፍ ክርስቲያን፡- *ዓለምን በእግዚአብሔር ዓይን የሚያይ፣ ለሕዝቦች ያለውን የእግዚአብሔርን ልብ የሚጋራና ጸሎቱን፣ ጊዜውን፣ ሀብቱን፣ ሙያውንና ሕይወቱን ለታላቁ ተልዕኮ የሚያቀርብ የክርስቶስ ተከታይ ነው።*

## 2. ዓለምን በእግዚአብሔር ዓይን ማየት

ዓለም አቀፍ ክርስቲያን ዓለምን፡- እንደ ፖለቲካዊ አገሮች ብቻ አያይም፣ እንደ ወገኖች፣ ነገዶች፣ ቋንቋዎችና ባህሎች ያያል፣ የወንጌል ዕድል ያላቸውንና የሌላቸውን ይመለከታል፣ በሕዝቦች መካከል ያለውን መንፈሳዊና ሰብአዊ ፍላጎት ይመለከታል።

## 3. ከጠባብ ክርስትና ወደ ዓለም አቀፍ እይታ

ጠባብ ክርስቲያናዊ እይታ፡- በራስ ፍላጎት ላይ፣ በቤተ ክርስቲያኑ ፕሮግራሞች ላይ ብቻ ያተኩራል። የራሱን ብሔርና ባህል ብቻ ያስባል። ተልዕኮን የሌሎች ሰዎች ሥራ አድርጎ ይቆጥራል። ያልተደረሱ ሕዝቦችን ችላ ይላል።

ዓለም አቀፍ እይታ፡- የእግዚአብሔርን ክብር ያስባል። ሕዝቦችን ሁሉ ያካትታል። በአካባቢና በዓለም ደረጃ ያስባል። በጸሎት፣ በመላክና በመሄድ ይሳተፋል። ከሌላ ባህል ሰዎችን ይቀበላል። ሌሎችን ለተልዕኮ ያነሳሳል።

## 4. የተልዕኮ ተሳትፎ መንገዶች

በታላቁ ተልእኮ ኀላፊነት ውስጥ ሁላችንም እየጸለይን ከታች ከተዘረዘሩት በአንዱ ወይም በሌላኛው መስክ የሥራ ድርሻችንን

እንወጣለን። በአንድ ወቅት በአንዱ፣ ሌላ ጊዜም በሌላኛው የተልእኮ ተግባር ልንጠመድ እንችላለን። ሆኖም በሕይወት ዘመናችን አራቱንም መለማመዱ መልካም ነው። እነዚህ አራት የሥራ ድርሻዎች "መሄድ"፣ "መላክ"፣ "ሌሎች የሕዝብ

ወገኖችን በእንግድነት መቀበል" እና "ማስተማበር" ናቸው። እያንዳንዱን በስፋት እንመልከት።

*1. መሄድ፡- "ታዲያ ያላመኑበትን እንዴት አድርገው ይጠሩታል? ስለ እርሱስ ሳይሰሙ እንዴት ያምኑበታል? ሰባኪ ሳይኖር እንዴት መስማት ይችላሉ?" (ሮሜ 10፥14) ወንጌል ያልደረሳቸው ሰዎች ወንጌል እንዲደርሳቸው የወንጌል መልእክተኞች መሄድ አለባቸው። ለዚህም ነው መጽሐፍ ቅዱስ "ሰባኪ ሳይኖር እንዴት መስማት ይችላሉ?" የሚለን። ለአንድ ሕዝብ ተመራጭ የሚሆነው የወንጌል መልእክተኛ ከዛው ሕዝብ አብራክ የወጣ ሰው ነው። ዛሬም ገና ወንጌል ያልደረሳቸው የሕዝብ ክፍሎች በኢትዮጵያ፣ በኤርትራ፣ በሶማሊያ እንዲሁም በጎረቤት አገሮች ስላሉ ሄዶ ወንጌልን የሚያበስር ሰው ይፈለጋል።*

*ለመሄድ እግዚአብሔር የጠራው ሰው የሚከተሉትን እርምጃዎች ቢወስድ ለአገልግሎቱ ያዘጋጁታል፤*

*♦ ሥራ ከፍሬ ይቀድማል፡- ባለህበት ቦታ ዛሬውኑ ወንጌልን በአጠገብህ ላሉ ሰዎች ሁሉ አካፍል። በጊዜው እግዚአብሔር ወደ ጠራህ የሕዝብ ክፍል ይወስድሃል። እስከዚያው ግን ባለህበት ቦታ አገልግሎትህን ጀምር።*

*♦ እግዚአብሔር ለተለየ ሕዝብ እንደጠራህ ከተረዳህ ፈጥነህ የተጠራህለትን ሕዝብ ቋንቋ ተማር፤ ባሕላቸውንም ማጥናት ጀምር።*

*♦ የተጠራህለትን ሕዝብ ለመመሳሰል አሁኑኑ አኗኗሩን መለማመድ ጀምር። ራስህን ሊመጣ ላለው የአገልግሎት ዘመን አዘጋጅ።*

*♦ ለአጭር ጊዜ (ከ2-4 ሳምንት) ወደ ተጠራህለት ሕዝብ ሄደህ ከሕዝቡ ጋር ቆይታ አድርግ። ራእይህም በዚህ የልምምድ ወቅት እየጠራ ይሄዳል።*

♦ ስኬታማ ለመሆን የሥነ መለኮት ትምህርት ቤት መግባት የሚጠቅምህ ከሆነ በጊዜ ተማር።

♦ ለተጠራህለት ሕዝብ እንዳንተው ሸክም ያላቸውን ሰዎች ፈልግ። ለተጠራህለትም ሕዝብ አገልግሎት ያላቸው አብያተ ክርስቲያናትና መንፈሳዊ ድርጅቶች አፈላልገህ ከእነርሱ ጋር ኅብረት ማድረግ ጀምር።

♦ ለአንተና ለአገልግሎትህ የሚጸልዩ 100 ሰዎች ወይም ቤተሰቦች መልምል።

♦ በገንዘብ ሊደግፉህ የሚችሉ ግለ ሰቦች፣ አብያተ ክርስቲያናትና መንፈሳዊ ድርጅቶች ካሉ አጠያይቅ። የተጠራህለት ሕዝብ ባለበት ስፍራ እየሠራህ ማገልገል ካሰብክ ደግሞ ይህንን ዓላማህን ሊረዱ የሚችሉ ሰዎች ፈልግ። ይህንን አሳብ በምዕራፍ ዘጠኝ በሰፊው እንመለከተዋለን።

♦ የጠራህ እግዚአብሔር ለአንተ የሚያስፈልገውን በጊዜው ስለሚሰጥህ በሰማኸው የእግዚአብሔር ድምፅ ሕይወትህንና አገልግሎትህን ምራ።

2. መላክ፦ "ካልተላኩስ እንዴት መስበክ ይችላሉ?" (ሮሜ 10፥15) ይህ ቃል የተላኩና የሚልኩ እኩል ድርሻ እንደሚወጡ ያሳየናል። ብዙ ጊዜ የሚሄዱት ጀግኖች፣ የሚልኩት ደግሞ ረዳቶች እንደሆኑ እናስብ ይሆናል። በእግዚአብሔር እይታ ግን የሚላኩም ሆነ የሚልኩ ሁለቱም እኩል ባለአደራዎች ናቸው። በእያንዳንዱ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ለመሄድ ጥሪ ካላቸው ይልቅ ለመላክ የተጠሩ ይበዛሉ። በርግጥም ላኪዎች አገልግሎታቸው ለመሄድ የተጠሩት ካላቸው አገልግሎት ጋር እኩል አስፈላጊ እንደ ሆነ ሊገነዘቡ ይገባል። ስለ መላክ ስንናገር የምናወራው ስለ ገንዘብ ብቻ አይደለም። ተላኪዎች የሞራል፣ የቁሳቁስ፣ የገንዘብ፣ የጸሎት እና የግንኙነት እገዛ ይሻሉ። አገልግሎታቸውን ጨርሰው በመመለስ ወደ ማኅበረ ሰባቸው ሲቀላቀሉም እንዲሁ የተለያየ እገዛ ያስፈልጋቸዋል።

3. እንግዶችን መቀበል፦ ሁላችንም በምንኖርበት በዚህ ምድር ብዙ ከእኛ የተለዩ የሕዝብ ወገኖችም አሉ። ይህም ቋንቋና ባሕላቸው ከእኛ የተለየ ሕዝብ ማለት ነው። እነዚህና እኛ በአንድ ከተማ መኖራችን አጋጣሚ ላይሆን ይችላል። እኛ ወንጌል እንድንነግራቸው ጌታ ወደ ከተማችን አምጥቷቸው ቢሆንስ? ወይም እኛን ወደ እነርሱ ከተማ አምጥቶን ቢሆንስ? እያንዳንዱን እድል ለወንጌል እንጠቀምበት።

4. ማስተማበር፦ አስተማባሪዎች ሥራቸው የእግዚአብሔርን የማይለወጥ ዓላማ ለቤተ ክርስቲያንና ለወንጌል አማኞች በማስተማር አብያተ ክርስቲያናትና አማኞች በእግዚአብሔር ዓላማ ውስጥ እራሳቸውን እንዲከትቱ መርዳት ነው። የእግዚአብሔር መንግሥት "ካድሬዎች" ናቸው ማለት ነው። አስተማባሪዎች በሕይወታቸውና በትምህርታቸው ሌሎች እንዲሄዱ፣ እንዲልኩ፣ እንግዶችን እንዲቀበሉ ወይም በማስተማበር ሥራ ላይ እንዲሰማሩ አርአያ ይሆናሉ። ሰዎችና አብያተ ክርስቲያናት ከሌሎች ተመሳሳይ ራእይ ካላቸው ጋር ግንኙነት እንዲኖራቸውና አብረው እንዲሠሩ የተቻላቸውን ያደርጋሉ። በዚህ ሁሉ ዋናው ሥራቸው አማኞች በእግዚአብሔር መንግሥት ውስጥ ትክክለኛ ቦታቸውን አግኝተው ፍሬያማ እንዲሆኑ መርዳት ነው።

# የዓለም አቀፍ ክርስቲያን ማጠቃለያ

1. መጸለይ፦ ለሕዝቦች፣ ለሚስዮናውያን፣ ለሰራተኞችና ለወንጌል በሮች መጸለይ።

2. መስጠት፦ ገንዘብ፣ ጊዜ፣ ችሎታ፣ ሙያ፣ ቤት፣ መኪናና ሌሎች ሀብቶችን ለተልዕኮ መስጠት።

3. መሄድ፦ ወደ ጎረቤት፣ ወደ ሌላ ባህል፣ ወደ ሌላ ከተማ ወይም ወደ ሌላ አገር መሄድ።

4. መላክ፦ ሰራተኞችን መለየት፣ ማሰልጠን፣ በጸሎት መሸኘት፣ በገንዘብ መደገፍ፣ በየጊዜው መገናኘት፣ ቤተሰባቸውን መንከባከብ።

5. እንግዶችን መቀበል፦ ከሌላ ባህል የመጡ ሰዎችን በፍቅርና በክብር መቀበል።

6. ማነሳሳት (ማስተማበር) mobilization፦ ቤተሰብን፣ ባልደረባን፣ መሪዎችንና ቤተ ክርስቲያንን ለታላቁ ተልዕኮ ማነሳሳት።